# የሕዝብን አመጽ የሚያሸንፍ ኃይል የለም!!

ይፍሩ ኃይሉ

በቅርቡ "ጎንደር፡ እሳቱን በሣት ያጠፋ ጀግና ነው" በሚል አረዕስት ባቀረብኩት ሐተታ ውስጥ የወልቃይት ጠገዴን የማነት ጥያቄ ተመርኩዤ ነበር። በዚያ ላይ የጎንደር ቁጣና ያስከተለው፤ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የተቀጣጥጠለ የሕዝብ ቁጣ በወልቃይት ጠገዴ የማንነት ጥያቄ ላይ ብቻ የተወሰነ ሣይሆን፤የመላው የኢትዮጵያን ሕዝብ የልብ ትረታንና ብሶት የነካ፡ በዉድም ሆነ በግድ ወያኔ ከሥልጣን መውረድ አለበት የሚል ነው ።

ከእንግዲህ የወያኔን የግፍ ቀንበር የምንሸከምበት ጫንካችን ተልጧልና ከትከሻችን በፍጥነት ይዉርድልን" እያለ ነው የሚጮኸው። ይህ ገና የመጀመሪያው "በቅቶኛልና የአዳምጠኝ" ጬኸት እንጂ ወያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደገሰለትን ያወቀው አይመስለኝም። እንደለመደው ያችኑ መርዙን፤ የከፋፍለህ ግዛ ዘዴውን እንዳይጠቀም ጎንደር ከኦሮሞው ከመራቁም በላይ " የኦሮሞ ሕዝብ ስቃይ የኔም ስቃይ ነው፤ የኦሮሞ ደም ሲፈስ የኔ ደም እንደፈሰሰ እቆጥረዋለሁ " እያለ ሰንደቁን አንግቦ ሲጮሕበት ወያኔ ወዴት ይሩጥ? ግን ያንኑ የፈረደበትን የትግራይን ሕዝብ ከማወናበድ አልጠቆጠበም። ጥቂት የአማራ ሆዳሞችና ፖለቲካ የተቀመጠው ኃይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ፤"ወልቃይት የትግራይ አካል ለመሆኗ ታሪክ ይመስክራል.." እያሉ ማንዛረጥ ጀመሩ።

የጎንደር ሕዝብና የኢትዮጵያ የታሪክ ምሁራን ከት ብለው ሳቁ አሁንም እየተንከተከቱ ነው። የወያኔ የቅርብ ወገኖቹና የቀድሞ ታጋዮቹ፤"የደም ዋጋህ ነው" እየተባለ፤ከድሃ እየተነጠቀ ዛሬ ባለቪላ፤ ባለብዙ መኪና፤ባለ ብዙ ኃብት ስለሆነ፤አብሮ ከወያኔ ጋራ ወልቃይት ጥገዴም ላይ ሆነ በሥልጣን ሙጥኝ ማለት ለኔ ይገባኛል ቢል አይፈረደበትም። ከሃያ አምስት ዓመት በፊት ለግሩ ጫማ ያልነበረው፤ዛሬ የግሩ ጫማ ከጣሊያንና ከስፔይን፤ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ የመጣ ነው።

የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት የወያኔ ተጋድይ፤ቁርሱን በልቶ ለምሳውና ለራቱ፤"ከየት ይመጣ ይሆን?" እያለ ሲጨነቅ የኖረ፤ዛሬ እምብርቱ እስኪገለበጥ ድረስ፤ በዚግኒና በጢብሲ፤በዶሮወጥና በምንቸት አብሽ ይቀበተታል። ጮማ እንደጎመን ይቆርጣል።የኢትዮጵያ ድሃ በጠኔ ሲሰቃይ፤ ወያኔ በቁንጣን ሲፈራገጥ ያድራል። እንኳን ቀምሶት ሰምቶት ያማያውቀውን ዊስኪና ብራንዲ፤ሻምፔኝና ዉድ የወይን ጠጅ ይጎንጫል።ጢንቢራው እስክዞር ድርስ ሰክሮ፤ በየቡና ቤቱ ሽንቱን በሱሪው ላይ እያንዠቀዠቀ፤ከኪሱ ሽጉጡን አውጥቶ በሰው መሃል ጥይት ይተኩሳል።

ጸጥታ አስከባሪው ጸጥታውን ያደፈርሳል። የዚህ ዓይነት ባለጌ ከዚህ ከተንጠለጠለበት ኮርቻ ላይ በፈቃዱ ይወርዳል ማለት ዘበት ነው። "ከዚህ ወርጄ እንደገና አጸበለስ ለቀማ?" ነው የሚለው። ይህ የሚወገደው በግድ ግንባር ግንብሩን እያሉ በማጋደም ብቻ ነው። የሚያሳዝነው፤ከአማራው፤ ከኦሮሞውና ከሌላውም ብሔረሶቦች ተውጣተው፤ከወያኔ ጋራ ለግል ጥቅም ሲሉ ብቻ፤ወገኖቻቸውን ሲገድሉና ሲያስገድሉ፤ከወያኔ ጋራ አብረው ሲዘርፉ የኖሩ ባንዳዎች ዛሬ መሬት ተከፍታ ብትዉጣቸው ይሻላል። ቀኑ የመሸው ለወያኔ ብቻ አይደለም ለነሱም ጭምር ነው። ዛሬ እነሱና ወያኔ የተሳፈሩበት መርከብ ይዟቸው ሊሰምጥ ከዉቂያኖስ ላይ እየዋለለ ነው።

የተነሳሁበት አረዕስት የሕዝብን አመጽ የሚያሸንፍ ኃይል የለም ብዬ ነው። ወያኔ እንደሚደነፋው ከሆነ ወያኔ ከሥልጣን ንቅንቅ አይልም የሚሉ እንደሚበዙ አውቃለሁ። ጎበዝ ይቻላል!!!።ወያኔ የሚለን፤"እስከጥርሴ የታጠቅሁ፤የሰለጠነ ወታደር ያለኝ፤የሃገሪቷን ቁልፍ ቁልፍ ቦታ ጨብጬ የያዝኩ፤ በምእራብ ሰሜን ወዳጄ፤ሱዳን ዋርዳያ ቆሞ ማንኛውም ጠላቴን፤ወደኔ አያሳልፍም።በምሥራቅ ደቡብ ብሄድ ጂቡቲና ሱማሌ በቁጥጥሬ ስር ናቸው።

በደቡብ ብሄድ እንደንዝርት የማሽከረክራት ኬንያ ከቃሌ አትወጣም። የመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ቢንጫጫ ባንድሙቀጫ አይደለምወይ?" ነው የሚለን። በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲያውን ሥራ በሚመለከት፤ የዘርፍኩትን ዶላር እያፈሰስኩ፤አሉ! የተባሉ ሎቢይስቶችን እየቀጠርኩ አፋቸውን አዘጋቸዋለሁ። ደግሞሳ፤ በአይሲስ ሆነ በአልካይዳ ለሚነጸርጸሩ ሀገሮች፤ለአሜሪካም ሆነ ለአውሮፓ ያለኋቸው እኔ መሆኔን፤በተለመደው በውሸት ፕሮፓጋንዳ ምን ያህል ከችግር ላይ እንደሆኑ፤በገዛ ሀገሬ ቦምብ አፈንድቼ፤ የሃገሬን ሕዝብ እየፈጀሁ፤የእሬሣ ክምር አሳያቸዋለሁ። ማነው ታዲያ እኔን ፍንክች የሚያደርገኝ፡" ባይ ነው።

የሕዝብ እንባ ጠባቂዎች ጬኸት የት ሊደርስ? ይለናል። ዕዉነትም ይህንን ቱልቱላ ላጣጣመው ፈሪ ጥጥቅ ያስፍታል። ግን እኮ ጎበዝ ቅድመ አያቶቻችን አድዋ ሲዘምቱ፤የሰለጠነና እስከ ጥርሱ ድረስ የታጠቀ ወታደር

አልነበራቸውም። “ሸፍነን፤ ድረስልን” የሚሉት ሱዳንም፤ ጂቡትም፤ሱማልያም አልነበሩም። ለሃያላን መንግሥታት የሚጮህበትን፤ዘዴውንም፤ መንገዱንም አያውቁትም ነበር። የነበራቸው ዕውነትኛ የሃገርና የወገን ፍቅር ነበር። የንበራቸው አንድነታቸውና መተማመናቸው፤ በይበልጥም የንበራቸው፤የማይገበረው ወኔና ቆራጥነት ነበር። ዓለምን ያስደነቀው የአድዋ ድል የተገኘው በጦር መሣርያ ብልጫና በሰለጠነ የጦር ኃይል አልነበረም። በየአንዳንዱ ጀግና የደም ፍሳሽና የአጥንቱ ክስካሽ የተገኘ ድል ነው።

ወያኔ “እንኳን ለምሣ ለቁርስም አይበቁኝ” ያለ በሚደነፋው ከንቱ ወሬ አንደናገጥ። ወያኔ የሚዋጋው ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋራ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ወዳጅነቱ እንጂ፤ጸቡ ለጠላቱ አይበጅም። ዛሬ በአስራ አንደኛው ሰአት፤ለሚገኝበት አጣብቂኝ ሁኔታ፤ወያኔ፤ለሥልጣን ያበቃውን፤የነፍስ አባቱን የሻብያን መንግሥት እየከሰሰና እየወነጀለ ነው። እራስክን ቻል ወያኔ!፤ ጸብህ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋራ ነው። እነደዛር በሰው ላይ አትቆለል። አልሰማህም እንዴ?
“ይተኩሏል እንጂ አዘልሎ ከጅ እንደ ዛር ብሰው ላይ ቢደረቡ አይበጅ።” ሲባል? ወደድክም ጠላህም አሁን ሃያ አምስት ዓመት ሙሉ” እኔ በመጣሁበት መንግድ ኑና ሞክሩኝ!” እያልክ ስትፎክር ኖረህ ዛሬ ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያን የምትወደውን የባሩድ ሽታና የጥይት ጩኸት ሊያጠግብህ ገና ትጥቁን እያስተካከለ እያለ ምነው ፈጥነህ ቅሌን ጨርቄን አበዛሕ? ትላንት “የአማራና የኢትዮጵያን ኦርቶዶስ ቤተክርስቲያን የጀርባ አጥንት ሰብሬ አድቅቄዋለሁ እያልክ ስትደነፋ፤ ዛሬ እንዴት የኢዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ትዝ አለችህ?ዛሬ በተራው ያ” ሸንታም አማራ”ብለህ የሰድብከው አማራ ዛሬ በተራው ሊያሸናህ ተዘጋጅቷል። በሰፈርከበት ቁና ልትሰፈር፤የዘራኸውን ልታጭድ፤የግፍ ምርትህን ልትሰበስብ ቀኑ ደርሷል። ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ወደዚች ዓለም መምጣቱ እነደማይቀር፤ያንተም በኢትይዮጵያ ሕዝብ ፊት ለፍርድ መቅረብህ አይቀሬ ነው። እንዴት? በለኝ።

ታሪክ አንብበሃል ብዬ እገምታለሁ። በታሪክ ውስጥ በቀደምትነት ከሚገለጹት የሕዝብ አመጾች ዉስጥ፤የፈረንሳይ፤የአሜሪካኑ፤ የቻይናው፤ የቀድሞው የ1917 የሶቬትና እንደዚሁም የሄሺያን፡(ሃይቲ) ሪቮሉሽን፤ ይጠቀሳሉ። እነዚህ ሁሉ አምጾች በጨቋኝ ገዢዎቻቸው ላይ ስለነበረ፤ያንን የበለጠና የታጠቀ ኃይል መቋቋም የሚችሉበት የወታደራዊ ብቃቱም፤የመሣሪያም ኃይል አልነበራቸውም። የነበራቸው፤ከታሰሩበት ሰንሰለትና ከተሸከሙት ቀንበር ለመላቀቅ በአንድነት በመተማመንና በቆራጥነት፤ የተከፈለውን ዋጋ ከፍለው እራሳቸውን ነጻ ማውጣት ነበር። የሁሉም የታቀደውን ግብ መተው የሃገራቸውን የፖሊቲካ መልከአ ምድር ለውጠዋል።

አሁን እንኳ በቅርቡ በሰሜን አፍሪካ፤በቱኒዚያ፤ሊቢያ፣ግብጽ የተከናወን ብናስታውስ ብዙም ሳንዛዛ እነዚህ ሶስት አገሮች ብቻ ይበቁን ነበር። እኔ ግን እንደ ምሳሌ ወስጄ፤ ነጥቤንም ያጠናክርልኛል ብዬ ስለምገምት፤በ1975 ዓ.ም የተደመደምውን የቪየትናምን ጦርነት ነው። እንድሚታወቀው የአሜሪካ በጦርነቱ ዉስጥ ጣልቃ መግባት የጦርነቱን እድሜ ያሳጥረዋል ተብሎ ነበር። በርግጥም አሜሪካ አለ የተባለውን የጦር ወታደሯን፤ በጥራቱን ሆነ በበላይነቱ ወደር የማይገኝለትን የጦር መሳሪያ እያስጣጠቀች ላከች።

ቆራጡ የቬትናም ሕዝብ የአሚረካንን የጦር አውሮፕላኖችንና ሄሉኮፐሮችን እንደቅጠል እያራገፈ ጣላቸው።፡ያን የሰለጠነ የጦር ወታደርም እንደዚሁ በራሱ መሳሪያ ቆሉት። ታላቂቷም አሜሪካ እጅ ወደላይ፤ በቃኝ በላ፤58000 ወታደር በላይ ሕይወቱን አጥቶ፤ስፍር ቁጥር የሌው ቁስለኛ(ከ200000 በላይ) ተሸክማ ወደአገሯ ተመለሰች። ይህ እንግዲህ የሕዝብ አመጽ የሚገታው ኃይል እንደሌለ ያሳያል።

በጡት አባታችሁ በአሜሪካ ወዳጅነት ብዙም አትመኩ። አሜሪካ እኮ የአጼ ኃይለጽላሴም፤ ለኢራኑ ሻህም፤ ለግብጹም ሙባረክ ወዳጅ ነበረች። ግን፡በዚያች አስራ አንደኛዋ ሰአት ታላቂቷ አሚኤሪካ ለአጼ ኃይለሥላሴም፤ ለሻሁም፤ ለሙባረክም አልደረሰችም። ምናልባት ለነ እንደናተ ያሉ ጥላቢሶች አሜሪካ ግድ ይኖራታል ብላችሁ ታስባላችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን የኛ አባቶች በራሳችን እንጂ፤በሌሎች መተማመንና መመካትን አላስተማሩንም።

ለናንተ ግን ለፈረንጅ ጭራ መቁላት አዲስ ነገር ስለአልሆነ ምንም አይመስላችሁም። ደግሞሳ በልመና የተራቀቃችሁ አይደላችሁም እንዴ?እናንተ በልመና የቃረማችሁት፤ከአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት እስከ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አስተዳደር ድረስ በርዳታ ይተገኘውን እንደሚበልጥብ ይታወቃል። ልዩነቱ የቀድሞዎቹ መሪዎች በሕዝብ ስም ለምነው ያመጧትን ለሕዝብና ለሃገር ነው ያዋሏት።፡እናንተ ግን እራሳችሁን አደለባችሁበት።

ከላይ ለማስረዳት እንደሞከርኩት የሕዝብ አመጽ በድል እንጂ በሽንፈት አይጠናቀቅም። የወያኔም ጸብ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋራ ነው። ወያኔ በኢትዮጵያ ሃብት በልጽጎ፤ እስከ ጥርሱ ድረስ ታጥቆ፤በሃብታችን አለኝ የሚለውን ጦሩን አስታጥቆ፤ማንነታችንን ለውጠ ትግሬዎች ሊያደርገን፤ለም መሬታችንን ወስዶ የትግራይ ሊያደርግ ቆርጦ መነሳቱን ዛሬ፤ጸሃይ የሞቀው፤ ሰው ያወቀው ምስጢር ሆኗል።የመይሳው ሃገር ተቆርጦ ከትግራይ ጋር ሲጠቃለል፤

የወልቃይትን ሕዝብ ትግሬ እንጂ አማራ አይደለህም ሲባል፤ እንኳን ጎንደሬውን፤ ጉራጌውን ከመሃል ሸዋ፤ ወላይታውን ከጋሞጎፋ፤ሲዳማውን ከሲዳሞ፤ኦሮሞን ከያለበት ደሙን ያፈላዋል።

መንዜውና መሬው፣ተጉለቴውና ሸንኮሬው በንዴት ቆሽቱ ያራል።እኔንም ይፋቴውን፤የወገኔ የጎንደር ሕዝብ በንቀትና በድፍረት የመይሳው ዘር፤ ዓይኑ ሲጓጎጥ ስመለከት፤እንደ አሞራ በረህ፤አርማጭሆ ገብተህ እደር ይለኛል።አሁን በወገናችን ላይ፤ ከኦሮሞ፤እስካፋር፤ከአርባምንጭ እስከ ሲዳማ፤ በየለቱ የሚፈጸመውን ግፍ ሳስበውና ሳሰላስለው፤አንዳንድ ጊዜ እንደሕልም ይመስለኛል። በዕዉነት እነዚህ ሰዎች ከትግራይ አብራክ የወጡ ኢትዮጵያውያን ናቸው ወይ? እያልኩ እራሴን እጠይቃለሁ። በጎንደር የሚደርሰውን ስቃይና መከራ ስመለከተው፤እራሴን ልስት ትንሽ ይቀረኛል። ደግነቱ ባለወኔው ያገሬ ልጅ በከተማ መሃል ጥይቱን እየዘራ፤ ወያኔ ዓይኑን አፍጥጦ እያየው፤ባጠገቡ እየፎከረ ሲሄድ ምንኛ ያኮራል።

የጎንደር አቀንቃኝ፡

" የጎንደርን ጀግና ከስቶ፤ ጠቁሮ ቢያየው፤
ወያኔ፤ ጎንደሬን፤ ጅማት ስጠኝ አለው።"
ወይ ዘመን ወይ ጊዜ ሁሉም ተለዋውጦ፤
ባንዳ አገር ይገዛል አርበኛው ተቀምጦ።
ወያኔ ደፋር ነው ላፉም ለከት የለው፤
የጎንደርን ጀግና ትግሬ ካልሆንክ አለው።
ወይ ልክ አለማወቅ አወይ አደፋፈር፤
በሰፈርው ቁና እሱም ሳይሰፈር፤
አጭደን ሳንከምረው፤እንደ ካብ ድንጋይ፤
የምን አስታራቂ የምን ገላጋይ፤
ሳናደራርበው አንዱን ባንዱ ላይ።"
እያለ ሲያቅራራ በኣይነ ሕሊናዬ ይታየኛል።፡

ዱሮ በልጅነቴ አባቴና ጉደኞቹ የአርበኝነት ጀብዷቸውን እያነሱ፤ አዝማሪ ቆሞ ግጥም እየተነገረው፤ ጀግናው ሰዉዬ አባረህ በለው!! እያለ ግጥሙን ሲደረድር፡ የሸነጠው እየተንጣ ቤልጅግና ዲሞትፈሩን እየተኮሰ ሲፎክር፤ሳይ “አይ ምነው ያን ጊዜ ተወልጄ ቢሆን ኖሮ!” እያልኩ ባለመታደሌ አዝን ነበር።ዛሬ ከአርባ አምስት ኣመት በኋላ ያ እመኘው የነበረው ወንድነትን ማስመስከሪያ ጊዜ ሲመጣ፤ከጎራው ከ8000 ማይልስ በላይ እርቄ በቴሌቪዥን መስኮት ብቻ እመለከተዋለሁ። በዚህ ወሳኝ ሰአት ኢትዮጵያ ዉስጥ ሆኖ የናት አገርንና የወገንን ፍዳ መካፈል መቻል ምንኛ መታደል ነበር!!

ወያኔ እንደ ድንፋታህ በርግጥም፤የአገሪቷን የጦር መሣሪያ ጥርግርግ አድርገህ መቀሌ ላይ ቆልለሃል። በሕዝብ ሃብት አለኝ የምትለውን ጦር አሰልጥነሃል። ግን ይኸ ሁሉ ለኛ ምናችንም አይደለም። “የኢትዮጵያን( የደርግን ጦር አሸንፌ ነው ከዚህ የደረስኩት” እያልክም አትቀደድ:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ከንድ አታውቀውም። በነጥርቅምቅሜ በደርግ መንግሥት ዉስጥ የነበሩት፤ ዕውነተኛ የኢትይጵያ ጅግኖች፤አንተንም፤ጌታህንም ሻቢያን አምርተውህ; በኤርትራ በረሃ ላይ ወድቀዋል። የተረፈው የደርግ ጦር የምትለው ላንተና ለሻቢያ በሰላይነት የተሰገሰጉ ሆዳሞችና ሱሪይቸውን ያወለቁ አተላዎች ናቸው።

አንተም፤ ጌታህም ሻቢያ እነዚህን ግርዶች፤በተቻለህ መጠን አኝከህ ሲበቃህ ተፋሃቸው። የሚገርመው፤ የድሮ ወዳጆችህ ያበላሹትን ለመጠገን ዛሬ፤ በየአለበት ጎንበስ ቀና ሲሉ ይታያሉ።(ኧረ እንዲያውም ሊወጉህ እየተዘጋጁ ነዉ ይባላል እና ተጠንቀቅ!!) እንደላም እየነዳህ፤ እሱም መንገድ እየመራህ አዲስ አበባ ሰተት አድርጎ ያስገባህ ወታደር፤ የደርግ አገዛዝ ያንገፈገፈው፤መሞትም፤ መግደልም የሰለቸው ሠራዊት ነው። አንተ ግን ሕሊና ቢስ ባለጌ በመሆንህ የኢትዮጵያን ሠራዊት በአንድ ቀን ዝንበር በትነህ ከሜዳ ላይ አፈሰስከው።

ታሪክ ይፋረድህ!!የኢትዮጵያ ሕዝብም መንገድ እየመራ፤ ሲርብህ እያበላ፤ ሲጠማህ እያጠጣ፤ ሲመሽብህ እያሳደረ ነው ከዚህ ያደረሰህ። ለውለታው ምን ከፈልከው? እርሱበርሱ እያጋጨህ እንዲተላለቅ ሞከርክ፤ ቤቱን በቡልዶዘር በላዩ ላይ አፈርስክበት።እናት አገሩን ኢትዮጵያን ያለወድብ አስቀረህ፤ኤርትራን አስገነጠልክ፤ የሚኮራባትን ባንዲራውን ጨርቅ ብለህ ተሳደብክ። ትምክህተኛ አማራ ብለህ ሰደብከው። ዘረኛ በመሆንህ በዘርህ ተደራጅ አልከው።

ቆራጡ አማራ በዘር መደራጀትን ላንተ ለዘረኛው ትቶ፤በኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ ይኸው ከዚህ ደርሷል።
ጸብህ ከዚህ ባለታሪክ ጀግና ሕዝብ ጋራ ነው። እንዳንተ በፈረንጅ ወዳጆቹ አይመካም፤አይመጻደቅም።

እንዳንተ ባለው የመሳሪያ ብልጫና ባሰለጠንከው ወታደር አይመካም። ሁለቱም የለውም። ግን በአስተሳሰቡና በሥነ ምግባሩ፤በሥነ ሥራቱ፤ በዲሲፕሊኑ ይበልጠሃል። ታንክና አውሮፕላን፤አዳፍኔና ባዙቃ የለውም። ግን አታስብ አንተ እያለህ እኛን የጦር መሣሪያ አይቸግረንም። አላማጣና ሊማሎሞ፤ ደንገዜና ጣርማበር፤ አድገን፤ አንተን የምናጠፋበት መሣሪያ እንዴት ይቸግረናል። የጦር መሣሪያህንና ሠራዊትህን ጭነህ ስትንከረፈፍ በናዳ ብቻ ጭፍልቀን እንፈጅሃለን።"የናቁት ያስረግዛል" ሲሉ አልሰማህም? ያንተን 50 ካሊበር ማሽን ገን እኛ የጉንዴ ጥይት በአፈሙዙ እየከተትን ከጥቅም ውጪ እናደርገዋለን።

በይበልጥ ደግሞ ይህ የሰለጠነ ጦር አለኝ እያልክ ጉራ መንዛቱን አቁመው። ሠራዊቱ የኢትዮጵያ ሠራዊት ነው። ምናልባትም ይቺ መልክት ታትማ ለንባብ ከመብቃቷ በፊት፤ጀግናው የኢትዮጵያ ሠራዊት ባንተ በራስህ ላይ የክላሹን አፈሙዝ እንደሚያዞር አልጠራጠርም። እንደነከርኩህ አመጹ የሕዝብ አመጽ ነውና ሁሉም ይረባረብብሃል።በየአቅጣጫው እንገጥምሃለን።እንሞታለን ግን ይዘንህ ነው የምንወድቀው። "ነብር አየኝ!!!"በል፤ እንደነቀርሳ በሁለንተናህ ገብተን እንደ ግንደ ቆርቁር ከውስጥ ነው የምንቦጠቡጥህ። አልቆልሃል።አላማጣን ዘቅዘቅ አትላትም። ጀግናው ወለዬ ዘብ ቆሟል።

በለስ ቀንቶህ ደሴን ብታልፍ፤ ኮምቦልቻን አትሞክራትም። ኤፍራታና ግድም፤ማጀቴና አንጾኪያ ይዘጋብሃል። ካራቆሬን ተዘቅዝቀህ፤መሃል ይፋትን ሰንጥቀህ ጣርማበርን አልፋለሁ ማለት ዘበት ነው። ከዚያ ግእባተ መሬትህ ይፈጸማል።ያደፈጠውን የይፋትን ነብር፤ አድብቶ የሚጠብቀውን የመሬን አንበሳ፤የመንዝን፤ የትጉለትና ቡልጋን ግሥላ ከጭኝቅላትህ እንዳይጠፋ።የመንጃርና የጅሩ፤የሸንኮራ፤ የየረርና ከረዩ ንስር አሞራ፤በቤልጅግ ጥይት ያንጠለጥልሃል። በአፋር በኩል አታስበው፤ እነሞት አይፈሬ አዘቦና እራያ የጥይት እራት ነው የሚያደርጉህ።

ወደ አፋር ምድር ዘቅዘቅ በትል፤ እንደተርብ እየነደፈ፤አሞሌ ጨው ቆፋሪ ነው የሚያደርግህ። ተሳክቶልህ በአዋሽ አቋርጠህ በኦሮሞ መሃል ለማለፍ ብትሞክር ጀግናው ኦሮሞ እያመረተ የጅብ እራት ነው የሚያደርግህ። "ከናንተ ተነጥዬ ነጻ ባወጣኋት አዲሲቷ የትግራይ ሪፐብሊክ፤በነጻነት እኖራለሁ ብትል፤ከኢትዮጵያ የዘረፍከው ሃብት ለአሥር ዓመትም አይበቃህ። ዙሪያውን ከበን ስለምናራዉጥህ፤ መሄጃ አጥተህ፤ እዚያው ደደቢት ዉስጥ፤ እነደ ሎጥ ሚስት የጨው አምድ ሆነህ ትቀራለህ፤ ወይም እንደ ጢስ ብን ብለህ ትጠፋለህ። ግን ከዚህ ሁሉ መዓት የምትድንበት መፍትሔ አለ። ይኸውም፡

ይህ ከምሆኑ በፊት ግን፤ ወጣት ልጆቹን የፈጀህበትን፤የሰድብከውን፤ያዋረድከውን፤ ከሃያ አምስት ዓመታት በላይ፤ ቁም ስቅዩን እያሳጣህ ያሰቃየኸውን፤ የትግራይን ሕዝብ ከዕግሩ ላይ ወድቀህ፤ይቅርታ ጠይቀህ መታረቅ አለብህ። ከዚያ እነዚህ የትግራይ መኳንንቶችና አዛዉንቶች፤ በሃገራችን ወግና ልማድ፤ባሕልና ሥረአት መሠረት፤ አንተን ወክለው፤ ቄስ፤ መነኩሴ፤ሼህና ሃጂ አስከትለው፤የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቁልህ።

ማሃሪውና ይቅር ባዩም የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ዕርግጠኛ ነኝ፤ይምርሃል፤ ይቅርም ይልሃል። ከዚያ ለሁለት አሥርት ዓመታት ተኩል በላይ ያጨማልከውን የተርመጠመጠ የፖሊቲካ ቡኮህን አጽድተው፤ጊዚያዊ መንግሥት አቋቁመው፤ ሕዝቦቿ፤በነጻነትና በኩልነት የሚኖሩባትን፤የሕግ የበላይነት የሰፈነባትን፤የሕዝብ የግል ሙብት የተከበረባትን፤ዲሞክራሲ የሚያብባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ፤ መልሰው፤ከጥንት የክብር ዙፋኗ ላይ ያስቀምጣሉ። እንደጨው ዘር የተበታተኑት ልጆቿ፤ ከያሉበት ተሰብስበው፤ በደስታ ወደ እናት አገራቸው ይመልሳሉ። አንተ ከተወገድክ፤ የኢትዮጵያም ሕዝብ መከራና ስቃይ ያቆማል።በኢትዮጵያም ሰላም ለሺ ዓመት ይሰፍናል።

በመጨረሻ ሳልነግርህ የማላልፈው፤አለኝ። "ባሳለፍኩት ሃያ አምስት ዓመታት ዉስጥ የአከማቸሁትን ዶላርና ወርቅ፤ብርና አልማዝ፤ ይዤ ወጥቼ፤አሜርካ፤ አውሮፓ፤ ኤዢያ፤ደቡብ ምሥራቅ እስያ፤ የትም ፤የትም ሄጄ ተደብቄ እየተደለቀቅሁ፤ ልጆቼን እያስተማርኩ እኖራለሁ።" የሚለውን ሕልምንህን አቁመው። እኛ ኢትዮጵያውያን፤እንድሜ ለድርግ መንግሥትና ለእናንተ ለአውሬዎቹ፤እኛ የሌንበት አገር የለም።

የትም ሂድ የት፤ ስምህን ቀርቶ ጾታህን እየለወጥክ ለመሮር አትከጅለው። ከገባህበት እየገባን፤እንደ ከርከሮ ግልገል ከተደበቅህበት ጉድጓድ ዉስጥ እየጎተትን አውጥተን፤ለፍርድ፤በኢትዮጵያ ሕዝብ በፊት እናቆምሃለን። ያ ባለረእዩ ጌታህ መለስ ዜናዊ በድንጋጤ ከው ብሎ በደህና ቀን አረፈላችሁ። ያ ቀላል የእንጨት ሽበት አቦይ ስብሃትም ዛሬ የተወለደበትን ቀን እየረገመ ይግኛል። ኧረ ለመሆኑ በረከት ሰሞንን ምን አምጣ ብላችሁ ነው ጎንደር የላካችሁት? በረከት እኮ ትግሬም፤ አማራም አይደለም፤ጎንደር ተወልዶ ያደገ የኤርትራ የውሻ ቡችላ ነው። ያን እለት ከጎንደር በሕይወት በመመለሱ በጣም ተናድጃለሁ። አንዲት ጥይት የሚያጣብቅበት እንዴት አንድ ጀግና ጠፋ?በሌላ በኩል ደግሞ ለንደሱ

ዓይነት ወደል አህያ ዕረፍት ነው። ቢቻል ኖሮ አንዱ ጠጋ ብሎ፤ የበረከትን መንጋጋ በቢልጅግ ሰደፍ ቢያላቅቅለት ኖሮ ግሩም ነበር።

የሁልችሁም ቀን ቀርቧል። ሰሌናችሁ ተርሷል፤መቃብራችሁ ተምሷል።አብራችሁ እንድመጣችሁ፤አብራችሁ አገር እንዳጠፋችሁ፤አብራችሁ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዳሰቃያችሁ፤ አብራችሁ የሃገር ሃብት እንደዘረፋችሁ፤በፍርድ ቀንም እንደዚሁ፤ እንዳማረባችሁ፤የኢትዮጵያን ሕዝብ ፊትለፊት መጋፈጥ፤ ያፈሰሳችሁት የንጹሃን ደም፤በሕዝብ ላይ የፈጸማችሁት ወንጀል፤ግፍና በደል፤ያለአግባብ ከኢትዮጵያ ደሃ ሕዝብ ላይ እየዘረፋችሁ፤ ያሚጠጣችሁት የሃገር ኃብት የዘረፋ ወንጀል፤ ግድ ይላል። ያነእለት እናንተን አያድርገኝ።

ኧረ ለመሆኑ፤የኢትዮጵያን ሕዝብ ምን ያህል ብትፈሩት ነው፤ምንም የጦር መሣሪያ ባልታጠቀ፤የአዲስ አበባን ሕዝብ በአሥርሽህ በሚቆጠር ሠራዊት፤በታንክና በብረት ለበስ መኪና፤የወረራችሁት?እነደዚህ የምትፈሩትንና፤ እሱም የሚጠላችሁን ሕዝብ እንዴት በማስገደድና በማስፈራራት ለመግዛት ትሞክራላችሁ?ኧረ የሰሚ ያለህ!!!!

ሞት ለወያኔና ለሆዳም ባንዳዎች!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ኢትዮጵያ በነጻነቷ ለዘለዓልም ትኑር!!

ይፍሩ ኃይሉ
Yhailu05@yahoo.com
August 22, 2016